## በዚህ የዳሰሳ ጥናት በመሳተፍ እንደሚተባበሩን ተስፋ እናደርጋልን።

### እኔ የተመረጥኩት እንዴት ነው?

በሬንቶን እና ሲያትል ቤተሰብን የአገለገሉ የቤቶች ባለስልጣን ንብረቶችን መርጠናል። በመንግስት ድጋፍ በቅናሽ በቀረቡ ቤቶች የሚኖሩ እድሜያቸው 6-44 አመት የሆኑ ሴቶችን እና 6-19 አመት የሆኑ ወንዶችን ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥያቄ እናቀርባለን።

### እኔ እገዛ ማድረግ የሚገባኝ ለምንድን ነው?

እኛ እንድንማር ይረዱናል:-

- ዳይት፣ በላስቲክ ምግብ ማብሰል፣ የቆዳ መንከባከቢያ እና ውበት መጠበቂያዎችን እንዲሁም የተባይ ማጥፊያዎችን መጠቀም ወደሰውነት በሚገባው የኬሚካል መጠን ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንደፈጠሩ።
- በመንግስት ድጋፍ በቅናሽ በቀረቡ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በግዛቱ ከሚኖረው ቀሪው ማህበረሰብ በበለጠ እነዚህ ኬሚካሎች በሰውነታቸው ውስጥ የሚገኙባቸው ስለመሆኑ።
- በሰዎች ሰውነት ውስጥ የእነዚህን ኬሚካሎች መጠን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል።

### ተሳታፊ በመሆኔ የማገኘው ነገር ይኖራል?

- ለአዋቂዎች የ25 ዶላር ቪዛ ካርድ ይሰጣል።
- 12-17 እድሜ ላላቸው ወጣቶች 15 ዶላር ቪዛ ካርድ ይሰጣል።
- እያንዳንዱ ቤተሰብ ለፀረ-ተባይ የሚኖረውን ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚረዳ መረጃ ያገኛል።
- ሁሉም ሰው ከማይዝግ ብረት የተሰራ የውሃ ጠርሙስ ይሰጠዋል።



### በዳሰሳ ጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑ:-

አዋቂዎችና ልጆች የቪዛ ካርድ ስጦታ ያገኛሉ። ሁሉም ሰው ከማይዝግ ብረት የተሰራ የውሃ ጠርሙስ ይኖረዋል።

### ለተጨማሪ መረጃ:-

በስልክ ቁጥር 1-877-494-3137 ይደውሉ ወይም ድረ-ገፅ http://www.doh.wa.gov/biomonitoring ይጎብኙ።

ይህ ብሮሸር በእንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ ራሽያኛ፣ ሶማሌኛ፣ ቬትናሚስ፣ ካንቦዲያን እና ትራዲሽናል ቻይኒዝ ቋንቋዎች ይገኛል።

ለአካል ጉዳተኞች፣ በተጠየቀ ጊዜ የዚህን ሰነድ በሌላ መልክ ማግኘት ይቻላል። ጥያቄ ለማቅረብ፣ በስልክ ቁጥር 1-800-525-0127 ይደውሉ (ቲዲዲ/ቲቲዋይ 711)።

WASHINGTON Environmental Biomonitoring SURVEY



# ሴቶች፣ ህፃናት እና ልጆች:-

## ስለ ፀረ-ተባዮች እና በላስቲክ ውስጥ ስለሚገኙ ኬሚካሎች ተጋላጭነት

እንድናውቅ ልትረዱን ትችላላችሁ።በዋሽንግተን ግዛት የጤና ዲፓርትመንት በቤታችሁ ስላሉ ኬሚካሎች ስለሚደረገው ጠቃሚ የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊ እንድትሆኑ ይጋብዛችኋል።

Washington State Department of Health

DOH 210-089 ማርች 2013 አማርኛ

## በዳሰሳ ጥናቱ እነዚህን አይነት ምርቶች ስለመጠቀምዎ ይጠየቃሉ።



ሜካፕ



የላስቲክ መያዣዎች



የላስቲክ የውሃ ጠርሙሶች



የታሸገ ምግብ



ፀረ-ተባዮች

3/2013 AMHARIC

## ከዚህ በመቀጠል ምን ይከናወናል?

በቅርቡ፣ የዋሽንግተን ግዛት የጤና ዲፓርትመንት የመስክ ሰራተኛ የሆኑ ሰዎች ከቤትዎ በመምጣት ስለ ዳሰሳ ጥናቱ ካብራሩልዎት በኋላ እርስዎም ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎት እንዳለዎት ይጠይቁዎታል። እነዚህ ሰራተኞችም ፎቶግራፍ ያለበት መታዎቂያ ይይዛሉ፤ እንዲሁም Washington State Department of Health የሚል ፅሁፍ ያለበት ገዋን ይለብሳሉ። ለመሳተፍ ከፈለጉ፣ በቤተሰብዎ ውስጥ ለመሳተፍ እንደሚፈልገው የሰው ብዛት፣ ጉብኝቱ እስከ 45 ደቂቃ ሊወስድ ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ፣ ሰራተኛው ተርጓሚ ሊያቀርብ ወይም በስልክ ሊያነጋግር ይችላል።

## ተሳታፊ ከሆንኩ ምን እንዳደርግ ልጠየቅ እችላለሁ?

- የፀረ-ተባይ እና የላስቲክ ኬሚካሎችን መኖር ለመመርመር ሁለት የሽንት ናሙናዎችን መስጠት።
- አስከምንወስደው ድረስ ሽንቱ በማቀዝቀዣ ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ።
- ስለ እርስዎ እና ቤትዎ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን መመለስ። እነዚህም ጥያቄዎች ስለተመገቡት ምግብ፣ ስለተጠቀሙባቸው የላስቲክ እቃዎችና የተባይ ማጥፊያ ስለመጠቀምዎ የመሳሰሉት ይሆናሉ።
- ይህ በሙሉ 30 ደቂቃ ያህል ይወስዳል።

## የእኔን ውጤት ማን ያውቃል?

ማን በዳሰሳ ጥናቱ ተሳታፊ እንደሆነ የሚያውቀው የጤና ዲፓርትመንት የዳስሳ ጥናት ቡድን ብቻ ነው። ሁሉንም መረጃ ምስጢራዊ እድርገን እንይዘዋለን። በምንሰበስበው ማንኛውም መረጃ ውስጥ ስም አይካተትም። ሪፖርት የሚደረገው ውጤትም በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት ቡድኖች አጠቃላይ ውጤት ነው።

## ለማወቅ የምትፈልጓቸው ኬሚካሎች ምን ምን ናቸው?

ፀረ-ተባዮች፣ ቢፒኤ እና ፕላትሌትስ።

- ፀረ-ተባዮች በህንፃዎች ውስጥና አካባቢ እንዲሁም በእርሻ ቦታ ነፍሳትን ለመቆጣጠር ጥቅም ላይ ይውላሉ።
- ባይስፌኖል ኤ (ቢፒኤ) በአደጉ ህፃናት ጡጦዎች እና የውሃ ጠርሙሶች፣ እንዲሁም በምግብ ሳህኖችና በመሳሰሉት ጠንካራ ላስቲኮች ውስጥ ይገኛል።
- ፕላትሌቶች ለስላሳና የሚተጣጠፉ ላስቲኮችን፣ ቬናይል ምረርቶችን እና የምግብ ማሸጊያዎችን ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላሉ። እንደ ሻንፖ፣ ሎሽን እና ሜካፕ አይነት የተወሰኑ የውበት መጠበቂያ እና የቆዳ መንከባከቢያ ምርቶች ውስጥ ይገኛሉ።

## የጤና ዲፓርትመንት ስለነዚህ ኬሚካሎች ለማዎቅ ለምን ፈለገ?

- የጤና ዲፓርትመንት በቅድመ-መከላከል እና በማስተማር ጤናን ለመጠበቅ ይሰራል።
- እነዚህ ከሜካሎች በለጋ እድሜያቸው ላይ ለሚገኙ እንስሳት ጎጂ እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ። በህፃናት፣ ልጆች እና 20-44 አመት እድሜ ባሉ ሴቶች ውስጥ እነዚህ ኬሚካች በምን ያህል መጠን እንደሚገኙ ማወቅ የሳይንቲስቶች ፍላጎት ነው።

## ለመሳተፍ ባልፈልግስ ምን ይከሰታል?

መሳተፍ የእርስዎ ምርጫ ነው። በማንኛውም ጊዜ ማቋረጥ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ወይም በቤትዎ ውስጥ ማንም ሰው ለመሳተፍ ፍላጎት ከሌለው፣ በዋሽንግተን ግዛት የጤና ዲፓርትመንትን በስልክ ቁጥር 1-877-494-3137 በመደዎል ማነጋገር ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በመንግስት ድጋፍ በቅናሽ በቀረበ ቤት ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ፤ ልጃገረዶች ወይም 6-44 አመት ውስጥ ያሉ ሴቶች ወይም 6-19 አመት ያሉ ወንዶች በቤት ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ፣ በመደወል ማሳወቅ ይችላሉ። ተሳታፊ ለመሆን ዘግይተውም ቢሆን ከወሰኑ፣ ይደውሉልን።

LowIncomeSurveyBrochureAM_CS6.indd 2 4/26/2013 2:58:25 PM